ውድቀት፣ የምግብ መጥፋት፣ የረሀብ መስፋፋት፣ የኑሮ ውድነት መጨመርና በአጠቃላይም የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በጣረሞት መያዝ በዚህ ዓይነት የሚቀጥል እንጂ የሚወገድ አይሆንም። ስለ ሞትና ጦርነት፣ ስደትና ሥቃዩም ይባባሳሉ እንጂ አይቀንሱም።

እነዚህ መንደር ምስረታ በሚል ፋሽስቱ መንግስት የሚያካሂደው ኢትዮጵያን ወደባሰ የሥቃይና የመከራ አዘቅት እየጨመረ ያለና የሚጨምርም ነው። ፀረ-ህዝብ እቅዶችን አየቁ ቁፈ ተግባራዊ ለማድረግ ለምቱ የሆነው ፋሽስታዊ መንግስት በህዝቡ የተባበረና የተጠናከረ ትግል እስካልተደመሰሰ ድረስ የፋሽስቱ መንግስት እነዚህ እቅዶችና እርምጃዎች ያው የምናውቀውንና ያንገፈገፈን የመከራ ኑሮ ከማጠናከር ሌላ የሚያመጡት አንዳች ሁኔታ ወይም አዎንታዊ ለውጥ አይኖርም።

በተባበረ ትግል ፋሽስቱን መንግሥት እንደምስስ!
ትግላችን አለጥርጥር ያሸንፋል!!